# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤ በስኳር ልማቱ ሒደት እነዚህ ኃላፊዎች "ሕዝባዊ መጠይቅ" ቢደረግላቸው?

Wednesday, 13 June 2018

ፋኑኤል ከንፉ

የብሄራዊ የፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ይናገር ደሴ እንደሚሉት፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች የሚገኘው ገቢ በአማካይ 3 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር ላይ ሲቆም፣ ከውጭ ምርቶችን ለማስገባት የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ ደግሞ ከ16 እስከ 17 ቢሊየን ዶላር ደርሷል። ስለዚህም፣ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በውጭ ንግድ መዳከም እና በውጭ ምንዛሪ እጥረት ሳቢያ አደጋ ውስጥ መግባቱ ተከትሎ የኢሕአዴግ ሥራአስፈፃሚ የፕራይቬታይዜሽን ውሳኔ ላይ ደርሷል።

ዶክተር ይናገር ደሴ "በተለይ" አሉ፣ "እንደ ስኳር ላሉ ፕሮጀክቶች የተወሰደው ብድር ደግሞ ወደ ምርት ሳይገባ እዳ መክፈያው ጊዜ ደርሷል" ብለዋል። ማን እዚህ ደረጃ ላይ እንዳደረሰው የሰጡት ዝርዝር መግለጫ የለም።

የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች ግንቦት 1 ቀን 2008 ዓ.ም በ2008 የበጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡት ሪፖርት፣ ተስፋ ቆርጠናል፤ ሕመም እየተሰማን ነው፤ ማለታቸው የሚታወስ ነው።

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ በበኩላቸው፤ "ኢትዮጵያ በዘረጋችው መጠነ ሰፊ የስኳር ልማት መንግስት ትምህርት አግኝቶበታል" ከማለታቸው ውጪ ተጠያቂ ያደረጉት፤ የፓርቲም የመንግስትም ኃላፊ የለም። ቀጫጭን ኃላፊዎችን ለመጠየቅ የተደረገው ሙከራ እንደተጠበቀ መሆኑን፤ ልብ ይሏል።

በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግስትና ገዢው ፓርቲ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶችን ሙሉ ለሙሉ ወደ ግሉ ባለሃብት ልናሸጋግረው ነው፤ የሚል መግለጫ ባሳለፍነው ሳምንት ከማውጣታቸው ውጪ፣ ለስኳር ልማቱ ክሽፈት ተጠያቂ ስለሚሆኑ የመንግስትና የፓርቲ ኃላፊዎች ያሉት አንዳች ነገር የለም።

ሰነዳቸው እንደሚለው፣ በልማታዊ መንግስት ፖለቲካ ኢኮኖሚ፣ የግል ባለሃብቱ ሊሰማራባቸው በማይችሉ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ መንግስት ጣልቃ እየገባ እንደሚያለማቸው በስፋት ሲናገሩ፤ አዳምጠናል። እንዲሁም መንግስት ከልማቱ ከሚያገኘው ትርፍ ጤነኛ ኪራይ በማደል ባለሃብቱና ዜጎችን የማብቃት ሥራዎች እንደሚሰራም፤ የገዢዎቹ ሰነድ ያሳያል።

መሬት ላይ ያለው እውነት እንደሚያሳየው፤ ገዢው ፓርቲና መንግስት በስኳር ልማቱ ከሽፈው፤ የግሉን ባለሃብት ሳያበቁ፤ ለልማቱ የተመደበውን የህዝብ ገንዘብ ለተመደበለት ዓላማ መዋል አለማዋሉን በሕግ የበላይነት ሳይዳኙ፤ የህዝብ ሃብት ወደ ግል ለማዞር ከውሳኔ ላይ ደርሰዋል። ምን ያህል ይሳካላቸዋል ወደፊት የምናየው ነው።

እኛ ጥያቄ ግን አለን? ይኸውም፣ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች በሪፖርታቸው እንዳስገነዘቡት፣ ኮርፖሬሽኑ ፋብሪካዎቹን ገንብቶና ምርት ኤክስፖርት በማድረግ ዕዳውን የመክፈል ኃላፊነቱን አልተወጣም። የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት ማሟላት አልቻለም፤ ግንባታዎቹን ለማከናወን 77 ቢሊዮን ብር የውጭና የአገር ውስጥ ብድር ተብድሯል፤ አንድም ፋብሪካ ወደ ምርት ማስገባት አልቻለም፤ በየአመቱ 13 ቢሊዮን ብር ዕዳ ለመክፈል ተዘጋጅቷል። በዚህ የክሽፈት ሒደት ውስጥ ኃላፊነት መውሰድ ያለባቸውን አካሎች በሕግ የበላይነት መጠየቅ ያልቻለ ገዢ ፓርቲ፤ እንዴት የህዝብ ሃብቶችን በአክሲዮን ድርሻ በማዘዋወር ልማት ሊያረጋግጥ ይችላል? እምነት እንዴት ይጣልበታል? ለሚሉት ከመንግስት ምላሽ የሚሹ ናቸው።

ለመንግስት ምላሽ እንዲሰጥባቸው የስኳር ልማቱን ተጠያቂነት መልክ ባለው ሁኔታ ማስቀመጡ ተገቢ ነው። ይኸውም፣ የመጀመሪያው ውድቀትና ተጠያቂነት የሚጀምረው፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ተከላ ግንባታዎች፣ የእርሻና የመስኖ ልማቶችን የተመለከተ ነው። ሁለተኛው፣ አስሩ አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ በተመለከተ ሲሆን፤ ሶስተኛው ከስኳር

ልማት ፈንድ ጋር በተያያዘ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ ወንጂ ስኳር ፋብሪካና በፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎችን ላይ ያስከተለው አሉታዊ ጫናዎችን የሚመለከት ነው።





አቶ ሶፊያን አሕመድ　　አቶ ግርማ ብሩ　　አቶ አለማየሁ ተገኑ

## በ"ልማታዊ መንግስት" አስተሳሰብ፣
## የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ታሳቢዎች

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካው በ "ልማታዊ መንግስታችን" ተጠናቆ ወደ ሥራ ገብቶ ቢሆን ኖሮ፣ በቀን 26 ሺ ቶን አገዳ የመፍጨት እና በአመት ከ 600 ሺ ቶን ስኳር የማምረት አቅም ይኖረው፤ ነበር። ከስኳር ምርት በተጨማሪ፣ በአመት 55 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሊትር ኢታኖል የማምረት አቅም ይኖረው፤ ነበር። በተጓዳኝም የተሰራው ግድብ ለመስኖ ስራዎች ልማት፣ ለእንስሳ፣ ለዓሣ እርባታ እና ከብቶች ለማድለብ አገልግሎት ላይ ይውል፤ ነበር። ከኃይል አቅርቦት አንፃር 120 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ይኖረው፤ ነበር።

ከሰው ኃይል አንፃር በመጀመሪያው የፋብሪካ ግንባታ 35 ሺ ሠራተኞች፤ በሁለተኛው የፋብሪካ ግንባታ ሲጠናቀቅ ተጨማሪ 35 ሺ ሠራተኞች በአጠቃላይ በስኳር ልማቱ ዘርፍ 70 ሺ ሠራተኞች እንደሚኖሩት ይጠበቅ፤ ነበር። የተንዳሆ ስኳር ልማትን በበላይነት ይመሩ የነበሩት፤ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቀድሞ ሚኒስትር አቶ ግርማ ብሩ እና ፕሮጀክቱን በማስፈጸም የቀድሞ የስኳር ድጋፍ ሰጪ ኤጀንሲ ዋና ዳሬክተር የነበሩት፣ አቶ በላይ ደቻሳ ናቸው። የመስኖና ውኃ ሥራዎቹን በበላይነት ይመሩ የነበሩት፣ አቶ አስፋው ዲንጋሞ በኋላ ደግሞ አቶ አለማየሁ ተገኑ ነበሩ።

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የውድቀት ሂደቶች በተመለከተ በሰንደቅ ጋዜጣ ቁጥር 558 በስፋት ያቀረብነው ቢሆንም፣ የተጨመቀው ዝርዝር ይህንን ይመስላል። የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ በኦክቶበር 2006 በቀድሞው የስኳር ድጋፍ ሰጪ ኤጀንሲ በኩል በአፋር ክልል ውስጥ አዲስ የስኳር ፋብሪካ ለመገንባት እንዲሁም በነባሮቹ ወንጂ እና ፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ስራዎች ለመገንባት ዓለም ዓቀፍ ጨረታ ማውጣቱ የሚታወቅ ነው።

የሕንድ መንግስት ለተንዳሆ አዲስ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ እና ለወንጂ እና ለፊንጫ ስኳር ፋብሪካዎች ማስፈፊያ 640 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር ፈቅዷል። ከተፈቀደው ብድር ጋር በተያያዘ ከአጠቃላይ የፋብሪካው ግንባታ እና ከፋብሪካዎቹ ማስፋፊያ ሥራዎች ውስጥ 85 በመቶ የሚሆነውን በሕንድ ኩባንያዎች እንደሚገነቡ በብድር ውሉ አስፍሮ ነው፣ ያበደረው። በጨረታውም፣ ከሃያ የሚበልጡ የህንድ ኩባንያዎች ተሳታፊ ነበሩ።

እ.ኤ.አ. በ 2008 በይፋ የተንዳሆ ፋብሪካ ተከላ ለአሸናፊው ኦቨርሲስ ኢንፍራስትራክቸር አሊያንስ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ የተሰጠ ቢሆንም፣ በ 2010 "ልማታዊ መንግስታችን" ለመረከብ ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም፤ ወፍ የለም።

የጨረታው አሸናፊ ከታወቀ በኋላ፣ በተደረገው ስምምነት የተፈቀደው ብድር ከተለቀቀበት ቀን አንስቶ በቀጣይ 30 ቀናቶች ውስጥ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ እንደሚጀመር ተገልጿል። የፋብሪካው ግንባታ በሁለት ዙር ተከፍሎ እንደሚከናወንም መገለፁ የሚታወስ ነው። የመጀመሪያው የፋብሪካው ምዕራፍ ግንባታ በ 2 ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል፤

የሁለተኛው የፋብሪካው ምዕራፍ ግንባታ ደግሞ የመጀመሪያው የፋብሪካው ግንባታ በተጠናቀቀ በቀጣዩ አንድ ዓመት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ ወደ ስራ እንደሚገባ ተገለፆም ነበር፤ ነበር ሆኖ ቀረ እንጂ።

በተደጋጋሚ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ ተቋማት ስለ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመጀመሪያው የጨረታ አሸናፊው ውጤት ለምን እንደተሰረዘ ጠይቀን እስካሁን ምላሽ፤ የሰጠን የለም። ለስኳር ፋብሪካ ተከላ የሚሆኑ ማሽነሪዎችን የሚያመርቱ ኩባንያዎች እያሉ፤ በምን አግባብ “trading house” ለሆነ ኩባንያ ጨረታው እንደተሰጠ እስካሁን ምላሽ፤ የለም። በጨረታው የተሳተፉት የህንድ ኩባያዎች በሀገራቸው ፍርድ ቤት ተካሰዋል። በሕንድ ፍርድ ቤት የተደረገው የክርክር መዝገብ ብዙ አመላካች ነገሮች ቢኖሩትም የተመለከተው የለም። ለጨረታ አሰጣጡ በተፈጠረ የፍርድ ቤት ክርክር የኢትዮጵያን መንግስት ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሏል። ይህም ሲባል፣ እ.ኤ.አ. ከ2008 እስከ 2010 በተከራካሪ ወገኖች በሕንድ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ተከላ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል።

ይኸውም፣ እ.ኤ.አ. በ2008 በሕንድ እና በኢትዮጵያ መንግስት የተንዳሆ ፋብሪካ ተከላ በተመለከተ የብድር ስምምነት ሲያደርጉ፣ የአንድ አሜሪካ ዶላር በኢትዮጵያ ብር የሚመነዘረው 9 ብር ከ50 ሣንቲም የነበረ ሲሆን፤ በሕንድ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ሲጠናቀቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሴፕቴምበር 1 ቀን በ2010 በሰጠው አዲስ የገንዘብ ምንዛሪ ተመን ለውጥ፤ የአንድ አሜሪካ ዶላር በኢትዮጵያ በ13 ብር ከ75 ሣንቲም ብር እንደሚመነዘር አስታውቋል። ከዚህ የገንዘብ ምንዛሬ ለውጥ ጋር በተያያዘ የተንዳሆ ፋብሪካ ተከላ ዋጋም በከፍተኛ ዋጋ እንዲንር ምክንያት ሆኗል።

ሌላው የምናቀርበው ጥያቄ፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ተከላ ውጤታማ ሳይሆን ለሁለተኛው ምዕራፍ ተከላ ክፍያ የፈቀደው አካል ማነው? የስኳር ኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጥቅምት 19/03/07 ለኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡት፣ የ2007 ዓ.ም. የነባር ፕሮጀክቶች ፊሲካል እቅዶች አንዱ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ፕሮጀክትን የተመለከተ ነበር። ባቀረቡት በሰነዱ ላይ እንደሰፈረው፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታ (13,000 ቶን በቀን) በነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ማምረት እንደሚጀምር፤ ይተርካል።


ሪፖርቱ አያይዞም፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካው ሁለተኛ ምዕራፍ ግንባታ ማናቸውም አስፈላጊ ቅደመ ክፍያዎች ለዋናው ኮንትራክተሩ መከፈላቸውን፤አስቀምጧል። በመጀመሪያው ምዕራፍ ወቅት ለቀጣዩ ምዕራፍ ግንባታ አስፈላጊው ዝግጅት በመደረጉ ይላል ሪፖርቱ፤ ሥራው በ2007 ዓ.ም የካቲት ወር ተጠናቆ መጋቢት 2007 ዓ.ም. ምርት እንዲጀምር፤ ያትታል።

እንዲሁም ሪፖርቱ፣ የመስኖ ግንባታና አገዳ ተከላ በተመለከተየተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመጀመሪያ ምዕራፍ 13,000 ቶን በቀን የመፍጨት አቅም ስላለው ይህን የሚመጥን 25,000 ሔክታር ላይ በመስኖ የሚለማ አገዳ ተክል ሽፋን ስለሚጠይቅ፣ ኮንትራክተሩ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በ2007 ዓ.ም. የልማት ዘመን የመጀመሪያውን ምዕራፍ 25,000 ሔክታር ያላለቁ የመስኖ መሰረተ ልማት አጠናቆ ያቀርባል። በተጨማሪም የ18,000 ሔክታር የጥናትና ዲዛይን ስራ ይሰራል፤ ይላል። በተያያዘም አገዳ ተከላ በተመለከተ የ2006 ተከላ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ሽፋኑ 18ሺ479 ሔክታር ደርሷል ይላል። እንዲሁም የአገዳ ተከላ በበጀት ዓመቱ (በ2007 ዓም.) 10ሺ 521 ሔክታር አገዳ ይተከላል ሲል ሰነዱ ያትታል። በተግባር የቀረበ የምርት ውጤት ግን የለም።


ጥያቄያችን፤ ለገዢው ፓርቲና ለኢትዮጵያ መንግስት፤ ኦቨርሲስ ኢንፍራስትራክቸር አሊያንስ ኩባንያ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የመጀመሪያ ምዕራፍ የፋብሪካ ተከላ ሥራውን እጅግ በወረደ አፈፃጸም ማከናወኑ እየታወቀ፣ ሁለተኛውን የተንዳሆ ፋብሪካ ተከላ ምዕራፍ ግንባታ እንዲያከናውን እንዴት ተፈቀደለት? ክፍያውስ እንዴት ተፈጸመ? በወቅቱ የነበረው 18ሺ 479 ሔክታር አገዳ የት አደረሳችሁት? ተጨማሪ ተተክሎ የነበረው 10ሺ 521 ሔክታር አገዳውስ ምን በላው?

ሌላው፤ በልማታዊ መንግስት ፖለቲካ ኢኮኖሚ መስመር ውስጥ ለማሳካት ያቀዳችሁት 600ሺ ቶን ስኳር፣ 55 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሊትር ኢታኖል፣ 120 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ፣ 70ሺ የሥራ እድል ፈጠራ እንደነበር ይታወቃል። የተፈለገው ውጤትም አልተላከም። ከዚህ አንፃር ገዢው ፓርቲ የልማታዊ መንግስት ተልዕኮን በመጨረስ ወደ ካፒታሊዝም እየተሸጋገረ ነው ተብሎ መውሰድ ይቻል ይሆን? ከአፈፃፀሙ አንፃር የሕዝብ ሃብቶችን ወደ ግል ይዞታ በማዘዋወር ይገኛል የሚባለው ውጤት እንዴት ይታያል?

የሕንድ ፓርላማ ልዑካን በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ አፈፃጸም ያሉትን መመልከቱ ጥሩ ነው። የፓርላማው አባላት ባቀረቡት ሪፖርት፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ተከላ የስራ አፈፃፀም ከሚጠበቀው በታች የወረደ በመሆኑ እሬታቸውን አቅርበዋል። አያይዘውም፣ ሕንድ በአፍሪካ ውስጥ ከቻይና ጋር ለምታደርገው የኢኮኖሚ ፉክክር በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ላይ የታየው የአፈፃፀም ደካማነት የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል ያላቸውን ከፍተኛ ስጋት፤ ለመንግስታቸው አስታውቀዋል።


አቶ አባይ ፀሐዬ


አቶ ሽፈራው ጃርሶ


ሚጀር ጀነራል ክንፈ ዳኘው

## አስሩ ስኳር ፋብሪካዎችን በተመለከተ

የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የሚያስተዳድራቸው የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች፤በደቡብ ኦሞ ዞን ኩራዝ አንድ፣ ኩራዝ ሁለት፣ ኩራዝ ሦስት፤ በአማራ ክልል በለስ አንድ፣ በለስ ሁለት፤ በአፋር ክልል ተንዳሆ አንድና ሁለት፤ በትግራይ ክልል ወልቃይት፤ በኦሮሚያ ክልል በአርጆ ደዴሳ የስኳር እና ከሰም ፕሮጀክቶች ናቸው። ይህንን የስኳር ልማት ተልዕኮ ለማስፈፀም በኃላፊነት ተቀምጠው የነበሩት አቶ አባይ ፀሐዬ፣ አቶ ሽፈራው ጃርሶ እና አቶ ወንድአወቅ አብቴ ናቸው።

በጥቅምት 19/02/07 የስኳር ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች ለኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት ላይ ስለ ፋብሪካዎቹ ግንባታዎች ዝርዝር መረጃዎች ማስፈራቸው የሚታወስ ነው።

ያቀረቡት ሰነድ እንደሚያሳየው፣ የፋብሪካ ግንባታ የ 2007 በጀት ዓመት ከስኳር ልማት ፈንድ እና ከአገር ውስጥ ብድር የተያዘ በጀትን በሚመለከት በሜቴክ እየተሰሩ ላሉት የበለስ አንድ እና ሁለት ብር 4 ነጥብ 26 ቢሊዮን፣ ለኩራዝ አንድ ብር 2 ነጥብ 30 ቢሊዮን በድምሩ ብር 6 ነጥብ 56 ቢሊዮን እንዲሁም ለተንዳሆ ምዕራፍ ሁለት ስኳር ፋብሪካ ግንባታ ብር 290 ነጥብ 76 ሚሊዮን፣ ለከሰም ብር 562 ነጥብ 5 ሚሊዮን፣ ለወንጂ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ቀሪ ክፍያ ብር 608 ነጥብ 33 ሚሊዮን እና በውለታ መሰረት የሚከፈል ለመለዋወጫ የሚከፈል ብር 1756 (15 ነጥብ 6 USD) ሚሊዮን ብር፤ 7 ነጥብ 2 ቢሊዮን የተጠየቀ ሲሆን፤ ብር 1 ነጥብ 94 ቢሊዮን በበጀት ዓመቱ መያዙን ገልጿል።

ኮርፖሬሽኑ በዚሁ መሰረት ይላል፣ ለበለስ አንድ እና ሁለት ብር 792 ሚሊዮን፣ ለኩራዝ አንድ 300 ሚሊዮን፣ ለተንዳሆ ብር 290 ነጥብ 76 ሚሊዮን እንዲሁም ለከሰም ብር 562 ሚሊዮን ብር እንዲያዝ ተደርጓል። እንዲሁም በውጭ ብድር ለሚገነቡት ለወልቃይት ብር 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን፣ ለኩራዝ 2 እና 3 ብር 4 ነጥብ 3 ቢሊዮን እና ለተንዳሆ ምዕራፍ ሁለት ፋብሪካ ግንባታ ብር 2.2 ቢሊዮን ጨምሮ በድምሩ ብር 12.9 ቢሊዮን ለፋብሪካ ግንባታ ተይዟል።

የነባር ፋብሪካዎች እና አዳዲስ ለሚገነቡ ፋብሪካዎች ለአማካሪ የሚከፈል ክፍያን በተመለከተ ለነባር ፋብሪካዎች የውጭ አማካሪዎች ብር 97 ነጥብ 7 (4 ነጥብ 89 USD) ሚሊዮን፣ አዳዲስ ለሚገነቡ ፋብሪካዎች ብር 120.98 (6 ነጥብ 04 USD) ሚሊዮን እንዲሁም ለአገር ውስጥ አማካሪዎች ብር 6 ነጥብ 11 ሚሊዮን በድምሩ ብር 208.12 ሚሊዮን ብር ለውጭ እና ለአገር ውስጥ አማካሪዎች የተፈቀደ ሲሆን፤ ይህም ከስኳር ልማት ፈንድ ከሚገኝ ገቢ እንደሚሸፈን ታሳቢ ተደርጎ የተያዘ መሆኑን ጠቁሞ፤ በጀቱ በዋና መ/ቤት በኩል እንዲያዝ ተደርጓል ይላል።

እንዲሁም በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አማካኝነት የሚገነባው የኦሞ-ኩራዝ ቁጥር 1 ስኳር ፋብሪካ መስከረም ላይ ተጠናቆ ህዳር 2007 ምርት ማምረት ይጀምራል ይላል። የኦሞ ኩራዝ 2 ፋብሪካ የፕሮጀክት ማስፈፀሚያ

ፋይናንስ ከቻይና ልማት ባንክ በብድር effective ሆኖ የመጀመሪያው ቅድመ ክፍያ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የተፈፀመ ስለሆነ በዚህ አግባብ ሁለቱም ፋብሪካዎች በ24 ወራት እንዲጠናቀቁ የታቀደ ስለሆነ፤ በበጀት ዓመቱ 49 በመቶ ሥራ ይከናወናል ብሎ ኮርፖሬሽኑ እንደሚጠብቅ በሰነዱ ላይ አስፍሯል።

አያይዞም በብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን አማካኝነት የሚገነቡት ሁለት 12,000 ቶን በቀን የመፍጨት አቅም ያላቸው ፋብሪካዎች ጣና በለስ ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 ታህሳስ ወር 2007 መጨረሻ እና በመጋቢት 2007 መጨረሻ እንደ ቅደም ተከተላቸው ተጠናቅቀው አገዳ ለመፍጨት ይዘጋጃሉ፤ ይላል። በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በመገንባት ላይ ላለው ስኳር ፋብሪካ የውሃ አቅርቦት እየተሰሩ ካሉት ካናሎች በመስመር ተገንጥሎ፤ ይገነባል ይላል።

ልብ ያለው ልብ ይበል፤ ከላይ የሰፈረው ሪፖርት በ2007 ዓ.ም. ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበ ሪፖርት ነው። ለማነፃፀር እንዲመች፣ የስኳር ኮርፖሬሽን የሥራ ኃላፊዎች ግንቦት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. የ2008 የበጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ባቀረቡ ወቅት፣ ተስፋ መቁረጥና ሕመም እየተሰማን ነው፣ ነበር ያሉት። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ነጭ ውሸት የበዛበት ሪፖርት፤ ከኮርፖሬሽኑ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንደሚቀርብ ነው።

በተለይ መጠየቅ ያለበት እና የሚቆጨው ጉዳይ፣ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካን ምዕራፍ አንድን ማስረከብ ላቀተው ለኦቨርሲስ ኢንፍራስትራክቸር አሊያንስ ኩባንያ፤የምዕራፍ ሁለትን የፋብሪካ ተከላ መፍቀድና ክፍያ መፈፀሙ ነው። በአጠቃላይ በስኳር ልማቱ ክሽፈት ተጠያቂ አካሎች አለመኖራቸው ነው። በዚህ ሁኔታ የህዝብ ሃብት የሆኑትን በሽርክና እንዲያዞርና ልማት እንዲያረጋግጥ እምነት እንዴት እንሰጠዋለን?

## የስኳር የልማት ፈንድ

የስኳር የልማት ፈንድ ተብሎ ስያሜ የተሰጠው የሂሳብ ቋት፣ ከመተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ ከወንጂ ስኳር ፋብሪካ እና ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ በሚገኝ ገንዘብ የሚንቀሳቀስ ነው። ስኳር ፋብሪካዎቹ ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነ ይተውላቸውና፤ ቀሪው ትርፋቸው በስኳር ልማት ፈንድ ስም ለተቀሩት ስኳር ፋብሪካዎች ልማት እንዲውል የታቀደ ነበር። ውጤቱን ስንመለከተው፣ አንድ ውጤታማ ፋብሪካ ሳይኖረን ነባር ፋብሪካዎች በውጭ ምንዛሪ እጥረት ከመለዋወጫ ውጪ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። እንደበፊት አሰራር ቢሆን ኖሮ፣ ነባር ፋብሪካዎቹ የመጠባበቂ የራሳቸው ገንዘብ ያስቀምጡ ነበር። ችግር ሲገጥማቸው ከመጠባበቂያ ቋት በማውጣት ይጠቀሙ ነበር። ዛሬ ላይ ብድር ወስዶ የማያውቅ መተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ ብድር ውስጥ ተዘፍቆ መስማት፣ ለምናውቀው ሕመሙ በጣም የከፋ ነው። ከላካይ በሌላቸው ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ውሳኔ መፈጠሩን ስለምናውቅ፣ ሕመሙ ድርብ ነው። የመጠየቅ አቅምም የለንም።

እንደመውጫ ግን ገዢው ፓርቲ የሕዝብ ሐብቶችን ወደ ግል ይዞታዎች ከማስተላለፍ በፊት፣ በተጠያቂ አካሎች ላይ የሕግ የበላይነት መኖሩን ማሳየት ይጠበቅበታል። ይህን ማድረግ ካልቻሉ፤ ሙስና ውስጥ ለመዘፈቅ የቆረጡና ወደፊት ምህረትን በሚጠብቁ አዲስ የፖለቲካና የመንግሥት ሹመኞች ቢሮክራሲው መወረሩ የማይቀር የቅርብ እውነታ ነው።

ጊዜው የእርቅና የምህረት ነው ከተባለ፤ ቢያንስ `public inquiry` (ለሕዝባዊ ጥያቄ መልስ መስጫ መድረክ) በማድረግ ከነበረው ስህተት ትምህርት በመውሰድ ቀጣይ ሃብት ማዳን ይቻላል፡፡ እንግሊዝ የኢራቅን ወረራ በተመለከተ ለቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትሯ ቶኒ ብሌየር ባመቻቸችው የ`public inquiry` ሁሉንም ነገር አውቃ፤ ወረራው ከተባበሩት መንግስታት መርህ ውጪ መሆኑን አረጋግጣለች፤ ተምራበታለችም፡፡ ቶኒ ብሌየርንም ከተጠያቂነት ነፃ አድርጋለች፡፡ እኛም ሀገር መካሰሱ ካልተፈለገ፤ ቢያንስ ይህንን ማድረግ ጠቃሚ ነው።■